የሰ/መ/ቁ/62370

ታህሣስ 26 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን - የቀረበ የለም

**ተጠሪዎች፡-** 1. አቶ ዕዮብ መስለ

2. አቶ ደምመላሽ አበዬ

3. አቶ ወንድማገኝ ይርጉ

4. አቶ ፍቃዱ ደጀኔ

} ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የሥራ ውል ማቋረጥን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪዎች ሥር ፍ/ቤት ከሣሽ ነበሩ፡፡ የሥር ፍ/ቤት አመልካች ከተጠሪዎች ጋር የነበረውን የሥራ ውል ከሕግ አግባብ ውጪ አቋርጧል በሚል ወደ ሥራ እንዲመልሳቸው ወስኗል፡፡ ከፍተኛው ፍ/ቤት ይህንኑ አጽንቷል፡፡

አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረበው አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች የ6 ወር ደመወዝ ከፍሎ ተጠሪዎችን ወደ ሥራ ይመለስ ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ስለመሆኑ ለመመርመር ተብሎ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

ተጠሪዎች ታህሣስ 1 ቀን 2003 ዓ.ም. የተጻፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪዎች በሰጡት መልስ በአመልካች በተያዘው የፕሮጀክት ሥራ ከ1994 ዓ.ም. ጀምሮ በተለያየ ቦታና የሥራ መደብ ሲሠሩ መቆየታቸውን ገልፀው የሥራ ውል ማደስ አስፈላጊ ነው ከተባለም ይሠሩ ከነበሩበት ሙያ ጋር በሚጣጣም መልኩ ባለመቅረቡ እንጂ ውል ለማደስ ፈቃደኛ መሆናቸውን ዘርዝረው በዚህም ምክንያት የሥራ ውል ማቋረጥ ከሕግ ውጭ ነው ተብሎ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ፍርድ በአግባቡ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች አቤቱታውን ከጠናክሮ የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተመለከተው ነው፡፡ እኛም ጉዳዩን ከተያዘው ጭብጥ አንፃርና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት የተቻለው አመልካች ከተጠሪዎች ጋር የነበረውን የሥራ ውል ለማቋረጥ ምክንያት ያደረገው ተጠሪዎች የውል እድሳት ውል ለመፈረም አልፈቀዱም አዲስ የውል ሁኔታን አቅርበዋል በሚል ነው፡፡

በሥር ፍ/ቤት ውሣኔ እንደተረጋገጠው ተጠሪዎች በአመልካች በተያዘው የፕሮጀክት ሥራ ውስጥ በነዳጅ ቀጅነትና በብየዳ ሥራ ላይ ይሠሩ እንደነበር እና የሥራ ውል ሊታደስ የሚገባ ከሆነም በዚሁ አግባብ እንጂ ጫኝ እና አውራጅ በሚለው የሥራ መደብ መሆን የለበትም የሚል ነው፡፡

አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው ተጠሪዎች ለውል እድሳት ያቀረቡት ሁኔታ ቀድሞ አልነበረም ተጠሪዎች የተቀጠሩት በዩኒቨርሳል ኤሌክትሪፊኬሽን አክሰስ ፕሮጀክት ውስጥ የተወሰነ ሥራ ለመሥራት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 10/1/ሀ መሠረት ነው፡፡

በመሠረቱ የሥራ ውል ባህሪ የሚወሰነው በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 9 እና 10 በተደነገገው አግባብ መሆኑ እሙን ነው፡፡ አሠሪው የሥራ ውል በአዋጅ አንቀጽ 10 ሥር በተደነገገው አግባብ የተፈፀመ መሆኑን ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡ ይህንን ማስረዳት ከቻለ ደግሞ የሥራ ውል ታደሰም አልታደሰ ሥራው ሲያልቅ ወይም ጊዜው ሲያበቃ የሥራ ውል ሊቋረጥ እንደሚችል አዋጁ በግልፅ ደንግጓል፡፡

በተያያዘው ጉዳይ አመልካች ተጠሪዎች የተቀጠሩበት የፕሮጀክት ሥራ ተጠናቋል የሚል ክርክር በአመልካች በኩል አልቀረበም፡፡ ስለሆነም የፕሮጀክት ሥራው አሁንም ቀጥሎ ያለ ስለመሆኑ መረዳት አዳጋች አይደለም፡፡ ስለዚህም ተጠሪዎች የተቀጠሩበት ሥራ አመልካች እንደሚለው በአንቀጽ 10/1/ሀ ሥር የሚሸፈን ነው እንኳ ቢባል የፕሮጀክቱ ሥራ ተጠናቋል፡፡ እስካልተባለ ጊዜ ድረስ የሥራ ውል አድሰዋል ወይም አላደሱም አሊያም ለማደስ ፈቃደኛ አልሆኑም በሚል ምክንያት ብቻ የሥራ ውልን ለማቋረጥ የሚቻልበት ሁኔታ በሕጉ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ስለሆነም አመልካች ያቀረበውን መከራከሪያ ነጥብ ውድቅ በማድረግ የሥር ፍ/ቤት የደረሰበት ድምዳሜ በሕግ ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚባልበት ምክንያት አልተገኘም፡፡

ስለዚህም ውሣኔው ባለበት እንዲፀና ብለናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 50103 ሰኔ 25 ቀን 2002 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 98347 በ30/02/2003 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡

2. በዚህ መዝገብ ላይ ህዳር 17 ቀን 2003 ትዕዛዝ ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ